# ሕግ-አልባነትን ሕጋዊ የሚያደርገውን አዋጅ መቃወም ፍትህና ነፃነትን የሚወዱ ዜጎች ሁሉ ግዴታ ነው

የግንቦት 7 ድምጽ ቁጥር 56 ርዕሰ አንቀጽ

ተቀናቃኞችን ለማጥቃትና ለዲስኩር ማሳመሪያነት ካልሆነ በስተቀር በሥራ ላይ ውሎ የማያውቀው የወያኔ ሕገ-መንግሥት በሰበብ አስባቡ ሲሸራረፍ ቆይቶ አሁን ‹‹የፀረ-ሽብርተኝነት አዋጅ›› የተሰኘው ደራጎን ገድሎ ሊቀብረው ተዘጋጅቷል።

የወያኔ መኩራሪያና ማጥቂያ ሕገ-መንግሥት ለበርካታ የሰብዓዊና የዜግነት መብቶች እውቅና የሚሰጥ ቢሆንም አንዳቸውም በሥራ ላይ ውለው አልታዩም። ይብሱኑ በተለያዩ ጊዜዓት በወጡ አዋጆች የሕገ-መንግሥቱ ማራኪ አንቀፆች ሲሸረሸሩና ሲናዱ ቆይተዋል። ለአብነት ያህልም ሙስና፣ አደገኛ ቦዘኔ፣ የባንክ ብድር፣ ፕሬስ፣ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችን በተመለከቱ የወጡ አዋጆችን መጥቀስ ይቻላል። እነዚህንና ሌሎችን ያልተዘረዘሩ አዋጆች ሕገ-መንግሥቱ እውቅና የሰጣቸውን መብቶች ሸራርፈዋል። የህጎች ሁሉ የበላይ ነው የተባለለት ሕገ-መንግስት በአዋጆችና ድንጋጌዎች ተሸርሽሮ አጥንቱ ብቻ በቀረበት ባሁኑ ወቅት እስከነአካቴዉ ገድሎ የሚቀብረው ‹‹የፀረ-ሽብርተኝነት አዋጅ›› ተረቅለት ለመጽደቅ የጣት ቆጠራ ብቻ ቀርቶታል።

ይህ ህግ ‹‹ሽብርተኝነት›› እና ‹‹የሽብር ተግባራት›› የሚሉ ጽንሰ ሃሳቦች የሰጠው ትርጓሜ ከመጠን በላይ በመለጠጣቸው ማናቸውም ዓይነት የፓለቲካ ተቃውሞ በሽብርተኝነት ለመፈረጅ ያስችላሉ። በዜጎች በተለይም በወጣቶች የተለመዱ የተቃውሞ መግለጫዎች ሁሉ በአዋጁ መሠረት ‹‹ሽብርተኛ›› ያስብላሉ። ከአፄ ኃይለ ሥላሴ ጊዜ ጀምሮ የሚታወቁት የተማሪዎች አድማ፣ መንገድ መዝጋት፣ ድንጋይ ውርወራ ከእንግዲህ ‹‹የሽብር ተግባራት›› ይሰኛሉ፤ ከአስራ አምስት ዓመት ጽኑ እስራት እስከ ሞት ድረስም ያስቀጣሉ። መለስና በረከት በኃይለሥላሴና በደርግ ጊዜ የነበራቸውን መንግሥትን የማወክ አንፃራዊ ነፃነት አንድ ሺህኛውን እንኳን ለዛሬው ወጣት ሊፈቅዱ አልፈለጉም።

በቅጣት ብዛት ለማሸማቀቅም በሽብርተኛነት የተፈረጀ ድርጅት አባል መሆን ቀርቶ የሞራል ድጋፍ እንኳን መስጠት ከአምስት እስከ ሃያ ዓመት ጽኑ እስራት የሚያስቀጣ ወንጀል ተደርጓል።

ይህ አዋጅ ወትሮውኑም ከፍትህ ጋር የማይተዋወቁትን የወያኔ ፍርድ ቤቶች ቅራቅቦዎችን በማስረጃነት የሚሰበስቡ የቆሻሻ ማጠራቀሚያ አድርጓቸዋል፡ ከእንግዲህ ፍርድ ቤቶች የስሚ-ስሚ ወሬዎችን፣ ተከሳሾችን በማሰቃየት የተገኙ ቃሎችን፣ በተጠለፉ ስልኮችና በዘረፋ የተገኙ ‹‹ማስረጃዎችን››፣ የራሳቸው የሰላዮችና የከሳሾቹ ሪፖርቶችን እና የመሳሰሉትን በአክብሮት በመመዝገብ ብይን የሚሰጥባቸው ጣቢያዎች ይሆናሉ።

በዚህ አዋጅ የዜጎች ሕይወት በፖሊስ መዳፍ ውስጥ ተጥሏል። ፖሊስ በሽብርተኝነት የጠረጠረውን ሰው በማንኛውም ጊዜ ሊያስር፣ ሊፈትሽ እና ንብረቱን ሊወርስ ሥልጣን

ተሰጥቶታል። ለአራት ወራት ጽኑ እስር ህጉ ከፖሊሱ የሚፈለገው ያሰረውን ሰው በየሃያ ስምንት ቀናት ወደ ፍርድ ቤት ብቅ እያደረገ ሌላ ሃያ ስምንት ቀናት የማስጨመርን ‹‹ልፋት›› ብቻ ነው።

ስለ ሽብር ተግባር መረጃ አለመስጠት ከሶስት እስከ አስር ዓመት ያስቀጣል። የተሳሳተ መረጃ መስጠትም እንደዚያው ከሶስት እስከ አስር ዓመት ያስቀጣል። በሌላ አነጋገር እያንዳንዱ ዜጋ መሪማሪ ፖሊስ ሆኖ ስለሚሰጠው መረጃ ትክክለኝነት ራሱ ምርመራ እንዲያደርግ ህጉ ያስገድዳል። ከዚህም በተጨማሪ መኪናም ሆነ ቤት ያከራየ ሰው የደንበኛውን ማንነት በሃያ አራት ሰዓታት ውስጥ ለአቅራቢያው ፖሊስ እንዲያስታውቅ በማስገገደድ የግለሰብ ነፃነትን ክፉኛ ይጋፋል።

ወያኔ ድሮም ቢሆን የህጋዊነትም ሆነ የይሉኝታ ለከት ኖሮት አያውቅም። አሁን ይፈቀድልኝ የሚላቸው ነገሮች ሁሉ ድሮም ሲያደርጋቸው የነበሩ ነገሮች ናቸው። ስለሆነም የፀረ-ሽብርተኝነት ህግ የፈጠረው አዲስ ነገር ቢኖር ለወያኔ ህገወጥ ተግባራት ህጋዊ ሽፋንን መስጠቱ ብቻ ነው።

ወያኔ ይህ አዋጅ መላውን ዜጋ በተለይም ደግሞ ተቃዋሚዎችን ያሽምቅቅልኛል ብሎ ተስፋ እንዳደረገ የሚያጠራጥር አይደለም። እውነታው ግን ተቃራኒው ነው። ይህ አዋጅ ከፀደቀበት እለት ጀምሮ በኢትዮጵያ ውስጥ ህግ አለ ማለት አይቻልም። በወረቀት ላይ እናውቀው የነበረው ሕገ-መንግሥትም በዚህ አዋጅ ተሽሯል። ይህ ደግሞ ትግላችንን ወደ አንድ ከፍ ያለ እርከን ያሸጋግረዋል። በፀረ-ሽብርተኝነት ሰበብ የታወጀውን ህግ-አልባነትን ከመላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ጋር በመሆን በትግላችን ወደ ሕገ-መንግሥታዊ ሥርዓት እንቀይረዋልን። ሕግ የሚባል ነገር ሁሉ ጠፍቶ አገራችን በፖሊስ የምትተዳደርበትን ሥርዓት በፍፁም መቀበል አንችልም። ሕግ-አልባነትን ሕጋዊ የሚያደርገውን አዋጅ መቃወም ፍትህንና ነፃነትን የሚወዱ ዜጎች ሁሉ ግዴታ ነው።

http://www.ginbot7.org/News_Paper/Ginbot_7_Dimts_Issue_No56.pdf